የመማር መብት የሠው ልጆች በሙሉ በተፈጥሮ ከተጐናፀፏቸው መብቶች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው መሆኑ አሌ የማይባል ነው፡፡ የመማር መብት ከሌሎች መብቶች የተለየ የሚያደርገው የኢኮኖሚ አቅማቸው ደካማ ለሆኑ አዋቂዎች፣ ህፃናት እና ሴቶች ራሣቸውን ነፃ የሚያወጡበት እና በህብረተሠቡ የዕለት ተዕለት ተግባራት ውስጥ እኩል ተሣትፎ የሚያደርጉበት ዓይነተኛ መንገድ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመማር መብት ተክብሮ እና ተሟልቶ ሲገኝ ለሌሎች ሰብዓዊ መብቶች አፈፃፀም እጅጉን ይረዳል፡፡



*የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት*
*በነፃና በግዴታ ለሁሉም!*

የመማር መብት እንደሌሎች ሠብዓዊ መብቶች ሁሉ በመንግስት ላይ የማክበር፣ የማስከበር፣ የማሟላት እና የማስፋፋት ግዴታን የሚጥል ሲሆን ይህም የሚመነጨው በዚህ ረገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመማር መብትን በተመለከተ ከሠፈሩ ድንጋጌዎች ነው፡፡ ኢትዮጵያ ተቀብላ ካፀደቃቸው እነዚህ ስምምነቶች ውስጥ የመማር መብትን በስፋት የሚያብራራ እና የመንግስት ግዴታን አንጥሮ ያስቀመጠው የአለም አቀፍ የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ስምምነት (ICESCR) ነው፡፡ የአለም አቀፍ የሠብዓዊ መብት መግለጫም በአንቀፅ 26 (1) ማንኛውም ሠው የመማር መብት እንዳለው እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ እና በግዴታ ለሁሉም ሊሠጥ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ የሴቶች እና የህፃናትን የመማር መብትን በተመለከተ በሴቶች ላይ የሚደረጉ ማናቸውም አድሏዊ ልዩነቶችን ለማስወገድ የተደረገው ስምምነት እና የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ላይ መብቱ ተዘርዝሮ እናገኘዋለን፡፡

ወደ ሀገር ውስጥ ህጐችም ስንመጣ የህጐች ሁሉ የበላይ ህግ የሆነው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትም በተለያዩ አንቀጾች ዜጐች ስላላቸው የመማር መብቶች ያትታል፡፡

ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ኮሚቴ የመማር መብትን በተመለከተ በጠቅላላ ትንታኔው (General Comment) ቁጥር 13 ላይ የመንግስት ግዴታዎችን ዘርዝሯል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ትምህርት ቤቶች በበቂ ቁጥር እና ጥራት ሊኖሩ ይገባል፡፡ ይህ ግዴታ በርካታ የትምህርት ቤት ህንፃዎችን ከማቆም ባሻገር ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚረዱ መገልገያዎች በበቂ ሁኔታ ማሟላትን ይጨምራል፡፡
- ትምህርት ቤቶች ሁሉም ሠው መማር እንዲችል ክፍት መሆን እና የተመቻቹ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም ሲባል በሰዎች መካከል ማንኛውም ተገቢ ያልሆነ ልዩነት ሣይደረግ ሁሉም ሠው ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል ሲሆን የገንዘብ አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑትንም ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ት/ቤቶቹ የሚገኝ ብት ርቀት ነዋሪዎች በቀላሉ ሊደርሱበትና ሊገለገሉበት የሚችሉበት መሆን አለበት፡፡
- ትምህርት እና የማስተላለፊያ መንገዱ በአካባቢው ህብረተሰብ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፡፡ በተለይም የአካባቢውን ባህል እና ሃይማኖት ትምህርቱ እና የማስተላለፊያ ዘዴው ሊፃረር አይገባም፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ የሚሰጠው ትምህርት የህብረተሠቡን ለውጥ እና እድገት ያገናዘበ እና በሂደትም ተለዋዋጭ ሲሆን ይገባዋል፡፡

ከፍ ብለው የተጠቀሱት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የመማር መብት በተመለከተ በመንግስት ላይ በየደረጃው ተለይቶ የተቀመጡ ግዴታዎችን ይዘረዝራሉ፡፡ ከነዚህም መንግስት ከገባቸው ግዴታዎች ውስጥ በከፊል ለመመልከት፡-

- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ እና በግዴታ ለሁሉም መስጠት፤
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሙያ ትምህርትን ጨምሮ ሁሉም የህብረተሠብ ክፍል ሊገለገልባቸው በሚችለው ቁጥር እና ቅርበት መዘጋጀት እና መሟላት አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የገንዘብ ዓቅም ለሌላቸው የነፃ ትምህርት እድል እና የገንዘብ ድጋፍ በሂደት ማሟላት፤
- የከፍተኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም በችሎታ መሠረት ክፍት መሆን እንዳለበት እና በሂደትም ነፃ የትምህርት ዕድሎች ማመቻቸት፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን መማር

ወይም ማጠናቀቅ ሳልቻሉ ግለሰቦች የመሠረተ ትምህርት መስጠት፤

- እኩል የትምህርት ዕድል ማግኘትን የሚያሣጡ በዘር፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ አመለካከት፣ በሃብት፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በትውልድ ወይም ሌሎች ምክንያቶች የሚደረጉ ልዩነቶችን ማስወገድ፤
- ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የመማር መብት እንዲኖራቸው ማረጋገጥ፤
- በማህበረሠቡ ስተገለሉ እና ለተጐዱ ወገኖች፤ ለምሳሌ እንደ አካል ጉዳተኞች፣ አነስተኛ የማሕበረሠብ ክፍሎች፣ ስደተኛች፣ እና ለመሳሰሉት ቅድሚያ የትምህርት ዕድል መስጠት፤
- ድንቁርናን እና ማህይምነትን ማጥፋት፤ የመሳሰሉት ይገኙበታል።



*የወደፊት አገር ተረካቢው ትውልድ*
*የመማር መብት ይጠበቅ*

መንግስት የመማር መብትን በተመለከተ ከፍ ብሎ የተዘረዘሩት ጠቅላላ እና ልዩ ግዴታዎች የተ ጣሉበት ቢሆንም እነዚህ ግዴታዎች በአንድ ሌሊት አሟልቶ ማቅረብ አለበት የሚል አመለካከት ሊኖር አይገባም። ለግዴታዎቹ መሠረት የሆኑት አለምአቀፍ ስምምነቶችም ሆነ ህገ-መንግስቱ በዚህ ረገድ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ በጀት በመመደብ መብቱን ለማሟላት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ እንዳለበት ያመለክታል። ከዚህም በተጨማሪ ምቹ የሆኑ የኢንቨስትመንት ህጐች እና ፖሊሲ ዎችን በማውጣት እና በማስፈፀም የግሉ ሴክተ ርን በማበረታታት ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ ማድረግ አለበት። ስለዚህም በቂ የገንዘብ አቅም የለም በሚል ምክንያት መንግስት እጁን አጣምሮ ቢቀመጥ አለምአቀፍ ስምምነቶች እና በህገ-መንግስቱ የተጣለበትን ግዴታ መጣሱ የሚያጠያይቅ አይሆንም።

★★★

*ይህን አጭር ጽሁፍ ያዘጋጀው አክሽን የባለሙያዋች ማህበር ለህዝብ (አፕአፕ) ነው። አፕአፕ በ1985 ዓ.ም የተቋቋመ አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን የተቋቋመበትም አላማ ህግና ሰብአዊ መብትን በመጠቀም የድሆችን በተለይ የሴቶችና የህጻናትን ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር ነው።*

*ለበለጠ መረጃ ከታች በተቀመጠው አድራሻ ያነጋግሩን።*

ስድስት ኪሎ፣ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል
በሚወስደው መንገድ ፤
ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትን አለፍ ብሎ፣
አዲስ የተሰራው የቴሌኮሚዩኒኬሽን ህንፃ ፊት ለፊት
ፖ.ሣ.ቁ. 12484፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ 251-11-1-243555፣ፋክስ 251-11-1243558
ኢ-ሜይል፡apap@ethionet.et
ዌብ ሳይት(ድረ-ገፅ): **http:**\\www.apapeth.org

# *የመማር መብት*

## አክሽን የባለሙያዎች ማህበር ለሕዝብ (አኘአኘ)